ቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ

**Coalition for Unity and Democracy Party (Kinijit)**

http://www.kinijitethiopia.org

e-mail kil@kinijitinternational.org Voice Mail/Fax 1-206-203-3974

ጋዜጣዊ መግለጫ ኪል_004/07

ጥር 19 ቀን፣ 1999ኣ.ም

# በአንድ ላይ እንነሳ

ለኢትዮጵያ ነጻነት፣ ለዳር ድንበር መከበር፣ ለህዝቡ አንድነትና ሰላም መጠበቅ ስትሉ አጥንታችሁን የከሰከሳችሁ፣ ደማችሁን ያፈሰሳችሁ የኢትዮጵያ ጀግኖችና አርበኞች፤

በወያኔ፣ ውሃ ቅዳ፣ ውሃ መልስ ዝብርቅርቅ የኤኮኖሚ ስርዓት ኑሯችሁ ከእጅ ወደ አፍ ላለፈውና በሸቀጥ ዋጋ ንረት፣ በኑሮ ውድነትና ለህይወታችሁ መሰረት የሆኑትን የዕለት ተዕለት አቅርቦቶች ማሟላት ላቃታችሁ አርሶ አደሮችና ሰርቶ አደሮች፤

በዘረኛው አገዛዝ የትምህርት ፖሊሲ ሰለባ ሆናችሁ የአፍላ ጉልበታችሁና የትኩስ አዕምሯችሁ ተጠቃሚ መሆን ያልቻላችሁ ወጣቶች፤

የህዝብ ብሶት መለኪያዎች፤ የወደፊቱ የሃገሪቱ ራዕይ ገላጮች የሆናችሁና ለጥይት ሳትበገሩ የህዝብ አለኝታነታችሁን በግንባር ቀደምትነት የገለጻችሁ የኢትዮጵያ ምሁራንና ተማሪዎች፤

ባለጠመንጃው ስርዓት በሚያራምደው ዕኩይ የግድያ ፖሊሲ ባሎቻችሁን ልጆቻችሁንና ወንድሞቻችሁን ያጣችሁ፣ ለእስር የተዳረጉባችሁ. የተሰደዱባችሁ የህብረተሰባችን ግማሽ አካል የሆናችሁ እናቶችና እህቶች፤

በአገዛዙ የስለላ መረቦች የፌጥኝ ተይዛችሁ የስራቱን ፍላጎት ማርኪያ እንድትሆኑና በወገኖቻችሁ ላይ ሳትወዱ በግድ መሳሪያ እንድትደግኑ የተደረጋችሁ የመከላከያና የፖሊስ አባላት፤

በአጠቃላይ በግንቦት 97ቱ ህዝባዊ ምርጫ በነቂስ ወጥታችሁ ማንነታችሁን የገለጻችሁ ነገር ግን ድምጻችሁን ተነጥቃችሁ ወገን ዘመዳችሁን በጥይት ተቀምታችሁ የሽብር ኑሮ እንድትኖሩ የተገደዳችሁ ኢትዮጵያውያን፤

አምባ ገነንነትን፣ ባርነትንና የጠመንጃ ፖለቲካን ለአንዴም ለመጨረሻ ጊዜም አሽቀንጥራችሁ ለመጣል የነበራችሁ ቁርጠኛነት በግንቦት 97ቱ ምርጫ ብልጭ ብሎ እንደጨለመ፣ በዴሞክራሲ ጭምብል ላለፉት 15 አመታት ታጅሎ የከረመው በግድያ ተወልዶ በግድያ ያደገ ስራዓትም ዕርቃኑን እንደቀረ ይታወቃል።

በዚህ ለመጀመሪያ ጊዜ በሃገራችን ታይቶ በማይታወቅ መልኩ ህዝብ መንግስትን በቃኝ ባለበት ሰላማዊ የፖለቲካ ተቃውሞ ምላሹ የንጹሃን ዜጎች ደም መፍሰስ፣ መጋዝ፤ መሰቃየትና መሰደድ፣ የህዝብ ውክልና ያላቸው መሪዎች መታሰር መሆኑ በግብር ታይቷል።

ግድያ ያልበገረውና ፍትህ የጠማው ወገን ግን ባገኘው አጋጣሚ ሁሉ ስርዓቱን መቃወሙን አላቋረጠም። ወጣት ተማሪዎች በየትምህርት ቤቶቹ ግቢ ያሰሙት የነበረው ተቃውሞ፣ የመስቀልና የደመራን በዓል አስታኮ ቁጣውን የገለጸው ምዕመን፣ እንዲሁም በታላቁ ሩጫ ውድድር ዕለት በሺዎች የሚቆጠረው ዜጋ ያሰማው የተቃውሞ ድምጽ፣ የተጀመረው የሰላማዊና የዴሞክራሲ መብቶች ትግል መቆሚያ ሊኖረው አለመቻሉን ነው።

ልጅ ወልደው ማስተማርን የሚወዱ የሃገራችን መሪዎች የደሃ ልጆችን ልብና አናት በጥይት ለመግደል ብቃት እንዳላቸው ቢያሳዩም በቃኝ አልገዛም ያለን ሰላም ወዳድ ኢትዮጵያዊ ልብና አዕምሮ ማንበርከክ አልተቻላቸውም።

ሶሻሊዝምን በዘር ፖለቲካ ለብጠው ግፋ በለው የሚሉት ወያኔዎች እንደዘመነ መሳፍንት ሁሉ ህዝቡን በጎሳ ከፋፍለው አንድነቱን ጭምር ሊቦረቡሩት ቢሞክሩም አልተሳካላቸውም።

የተሸፋፈኑበት በዴሞክራሲ ቀለም የተዘፈዘፈ ከፈን በግንቦቱ ህዝባዊ ድል ከፊታቸው ላይ እንደተገፈፈ ገሃድ ቢሆንም፣ በህዝብ ሳይሆን በገንዘብ ለጊዜው መቆየትን የመረጡት አምባ ገነኖች፣ እናት አገርህ ተደፈረች ብለው የወገኖቻችንን ደም በባዕድ መሬት ላይ በማስፈሰስ እንቁዉን ሃቅ በብርቅርቁ መለወጥ አልተቻላቸውም።

እነኝህ ሃገር በቀል ጨካኞች በጥይት በሳንጃና በገመድ የተንቀሳቀሱበት የጥፋት ተልዕኮ ወጣቶችን፣ ተማሪዎችንና የሰባዊ መብት ተሚጋቾችን፣ የነጻው ፕሬስ ወገኖችን፣ የሲቪክ ማህበረሰብ አባላትን፣ ህጻን አዛውንትን ሳይመርጡ በጅምላ ቢፈጁም፣ ህዝብ ውክልና የሰጣቸውን የሃገር አለኝታዎች እግር ተወርች ቢያስሩም፣ የብዙሃኑን እምቢታ ሊያፍኑ በፍጹም አልተሳካላቸውም።

የወያኔ ኢሃዴግ አምባ ገነኖች ህዝብ በድምጹ የመረጣቸውን መሪዎቹን በመግደልና በማሰር በሚወስዱት ግፈኛ እርምጃ የነጻነቱን ትግል ግለት መቀነስ ፈጽሞ አልሆነላቸውም።

ኮምኒዝም በሞተ በማግስቱ በህዝብ ጫንቃ ላይ የተቀመጡት አብዮታዊ ዴሞክራቶች በዘረኛና ፋሽስታዊ ዘይቤአቸው ሊቀጥሉ ሁኔታው ፈጽሞ አልተመቻቸላቸውም።

በቃኝ ባዩ የኢትዮጵያ ህዝብ ሆይ!

የተነሳህለት የአልገዛም ባይነት ተጋድሎህ ዕልባት ያገኝ ዘንድ፣ ለዘመናት ታልመው የነበረው የዲሞክራሲ ስርዓት ግንባታ እውን ይሆን ዘንድ፣ ትመኘው የነበረው የኖረው የሃገርህ ታሪካዊ አንድነት እንደነበረ ይቆይ ዘንድ፣ ድምጽህን አናስነጥቅም፣ የገባነውን ቃልኪዳን አናፈርስም ብለው ለእስር የተዳረጉትን መሪዎችህንና የህዝብ አለኝታዎች የማስፈታት ዘመቻው አሁን ነው።

ሃገርህ ኢትዮጵያን ወደዜጎች እስር ቤትነት የለወጠውና የዴሞክራሲያዊ ስርዓትዋን እመርታ ያጨነገፈው የወያኔ ኢሃዴግ አገዛዝ ዛሬም ለዴሞክራሲና ለሰላም ሊገዛ የማይወድ ስርዓት እንደሆነ ልናስረዳህ እንወዳለን፣

ዘረኛው አገዛዝ የተወሰኑ የህብረተሰብ ክፍሎችንና ጠመንጃውን ብቻ መከታ በማድረግ፣ የተመረጡ የህዝብ ተወካዮችን አስሮና ገድሎ ዛሬም አገዛዙን በተለመደው ዘይቤ መቀጠል ወምረጡን ልንገልጽልህ እንወዳለን፣

አገዛዙ ከኢትዮጵያ ህዝብና ከአለም አቀፉ ሰላም ወዳድ ህብረተሰብ የቀረበለትን ጥሪ በመናቅ የህዝብ ተወካዮችን በህግ ከለላ ስም ማሰር ማጉላላት መምረጡን፣ በታማኝ ካድሬዎቹ አማካይነት የሃሰት ምስክርና ዳኝነት በማሰናዳት ፍትህ ለማዛባት እንደሚጥር በይፋ እየታየ ነው::

በመሆኑም ከዚህ በኋላ የሚኖርህ አማራጭ እጅ ለእጅ ተያይዞ ለነጻነትና ለዴሞክራሲ የጀመርከውን ሰልማዊ ትግል አጠናክሮ መቀጠል ብቻ ይሆናል።

ይህ ሰላማዊ ትግል በሃገር ውስጥና በውጭ ሃገር በሚኖሩ ኢትዮጵውያን እንዲሁም ተቃዋሚ የፖለቲካ ሃይሎች በአንድነት « የሃሰት ውንጀላ ያብቃ! የቅንጅት መሪዎችና ሌሎችም የህሊና እስረኞች በአስቸኳይ ይፈቱ! ብሄራዊ እርቅና የሰላም ጉባኤ በአስቸኳይ ይደረግ!» በሚሉ ወቅታዊ መፈክሮች ስር በሚካሄድ ባለ ዘርፈ ብዙ፣ አለም አቀፍ እንቅስቃሴ መሆን ይገባዋል።

ወያኔ ኢሃዴግ በግፍ አስሮና የሃሰት ምስክሮች አሰባስቦ ባቀነባበረው የፍርድ ሂደት እየተንገላቱ የሚገኙትን የቅንጅት መሪዎች፣ ጋዜጠኞችና የሲቪክ ማህበራት ተወካዮችን የማስፈታት ተልዕኮ በማድረግ በቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ ፓርቲ የተጀመረዉ ሥራ በተቀነባበረ ሁኔታ እንዲቀጥል የሁሉም ዜጋ ያልተቆጠበ ተሳትፎን ይጠይቃል::

ይህ የተቃውሞ እንቅስቃሴ መሪዎቻችንን በማስፈታት ብቻ የሚያበቃ ሳይሆን በሃገራችን እንዲገነባ የታገልንለትና አኩሪ መስዋዕትነትን የከፈልንበት ዴሞክራሲያዊ የፖለቲካ ስርዓት እውን እስኪሆን ተጠናክሮ የሚቀጥል ይሆናል።

ይህንን የተቃውሞ እንቅስቃሴ ተግባራዊ ለማድረግ በሃገር ውስጥም ሆነ በውጭ ሃገር የምንገኝ የህዝብ ወገኖች በፖለቲካ በዘርና በሃይማኖት ሳንከፋፈል፣ እጅ ለእጅ ተያይዘን መነሳት ይኖርብናል።

የወያኔ አገዛዝ የፈጠራ ክሱን ሰርዞ፣ የታሰሩ የህዝብ ልጆችንና መሪዎችን ካለምንም ቅድመ ሁኔታ ፈትቶ ለህዝባችን ፈቃድና ለህግ ራሱን እስከሚያስገዛ ድረስ ተባብረን እንድንታገል ጥሪያችንን እናቀርባለን።

የተባበረ ህዝብ ምንጊዜም አሸናፊ ነው።

## ቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ (ቅንጅት)